# Learning by Ear 2013

# መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ - ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWO: **የሁለት ክፍሎች ግጭት**

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITORS: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ምህረት GOES TO BONGO ACADEMY**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ዘበኛ (M, 55)**
- **አቶ ጃለታ (M, 45)**

**SCENE 2: አቶ ሙላቱ RECEIVES A CALL FROM HIS SISTER ወይዘሮ ለምለም, WHO LIVES ABROAD.**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **ወይዘሮ ለምለም (F, 40)**

**SCENE 3: ምህረት AT PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ OFFICE**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**
- **ምህረት (M, 15)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

- አቶ ጃለታ (M, 45)

**SCENE 4: አቶ ሙላቱ AT HOME WITH HIS WIFE ወ/ሮ ሉሊት**

- ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)
- አቶ ሙላቱ (M, 45)
- ምህረት (F, 15)

1. **INTRO - NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ አዝናኝ ትምህርታዊ ድራማ ክፍል ሁለት ነዉ። ባለፈዉ ክፍል ጭዉዉት ሶስት አዳጊ ጀግኖቻችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋውቀናል፡፡ ለማስታወስ ያህል…የ16 ዓመቱ ንጉሴ ጃለታ በቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ዓመት ትምህርቱ የሚያስፈልገውን የትምህርት ቤት ቁሳቁስ ለመግዛት ከእናቱ ጋር መደብር ሄዶ ነበር፣ በተለይ ለእናቱ ቀኑ አስደሳች ነበር፡፡

2. **ወይዘሮ ዘውዲቱ (EP 01, LINE 42):** "የኔ ልጅ በቦንጎ አካዳሚ! እምም፣ ጓደኞቼን አግኝቼ ስለ አንተ እያነሳሁ በጉራ ላቅራራባቸው ቸኩዬአለሁ።"

3. **ንጉሴ (EP 01, LINE 43):** "እማ …"

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዳንኤል ካሳሁን ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርት ሰብለ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝቶአል። ሊኖር የመጣበት የአዲሱ  ሀገር አቀባበል ሞቅ ያለ አልነበረም።

4. **ሰብለ** (EP 01, LINE 61): “እና የዚህ ሀገር ነዋሪ አይደለህም፣ ልክ ነኝ?”
5. **ዳንኤል** (EP 01, LINE 62): “ትክክል፤ ከላቦሪያ ነዉ የመጣሁት” (...)
6. **ሰብለ** (EP 01, LINE 63): "“አሀ፤ መልካም፤ እና የትምህርት ቤት ክፍያውንም ይዘሀል?”

ለምህረት ሙላቱ ደግሞ በሀገሪቱ ምርጥ ከተባለው ትምህርት ቤት፣ ከቦንጎ አካዳሚ የነጻ ትምህርት እድል እንዳገኘች ስታውቅ ቀኑን በህይወቷ ምርጡ አድርጋ ወስዳዋለች። ቤተሰቦቿ ግን ደስታዋን አልተጋሩም። በኋላ ሌሊት ላይ ያወሩትንም ሰምታለች።

7. **ሙላቱ** (EP 01, LINE 72): “አሁን ምህረት የ15 ዓመት ልጅ ናት። የሆነ ሰው ሚስት ለመሆንም  ደርሳለች። ከዚህ በተጨማሪ ስለምናገኘው ጥሎሽ ሁሉ አስቢ!”
8. **ሉሊት** (EP 01, LINE 71): “ አይሆንም፣ ሙላቱ! ያንን ምህረት ላይ ማድረግ አንችልም። አይገባትም! ”
9. **ሙላቱ** (EP 01, LINE  76): “ሉሊት፣ ወስኛለሁ!”

አሁን “ የሁለት ክፍሎች ግጭት” የተሰኘውን ሁለተኛ ክፍል ድራማ ለማድመጥ ተዘጋጁ። ማታ ምህረት በወላጆቿ መካከል የተደረገውን ውይይት በጸጥታ ካደመጠች በኋላ ማድረግ የምትችለው አንድ ነገር ብቻ እንደሆነ አውቃለች። ይኸዉም በማለዳ ከቤቷ ሹልክ ብላ ወጥታ በቀጥታ ወደ ቦንጎ አካዳሚ መሄድ ነበር።

**SCENE 1: ምህረት GOES TO BONGO ACADEMY**

10. **ATMO: BONGO HIGH OUTSIDE (NO BREAKTIME), TRAFFIC IN BACKGROUND**

11. **ምህረት:** (pleading with security ዘበኛ) እባኮ ያስገቡኝ! ይኸዉሎ- የነገርኮት ሁሉ እዉነቴን ነው-ቦንጎ አካዳሚ ተቀብሎኛል። ደብዳቤውም ይኸው፣ እራሶ ሊያነቡት ይችላሉ!

12. **ዘበኛ:** (strong African accent, faulty grammar) አንቺ ልጅ፣ ልታጃጅይኝ እየሞከርሽ ነው?

13. **ምህረት:** ምን አሉኝ?

14. **ዘበኛ:** ማንበብ ይችላል ብሎ ማን ነገረሽ? መቶ ጊዜ ነግሬሻለሁ። ወላጆችሽን እስክታመጪ ድረስ እንድትገቢ አልፈቅድልሽም።

.

15. **SFX: CAR ARRIVES NEXT TO THEM, HONKS THE HORN**

16. **ምህረት:** እባክዎ የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህር አንድ ጊዜ ማግኘት እፈልጋለሁ! ያንን ብቻ ነው የምጠይቅዎ ።

17. ዘበኛ: ወደዚያ ዞር በይ ብየሻለሁ። ስራዬን እያስተጓጎልሽብኝ ነው።

18. **SFX: CAR WINDOW TURNED DOWN**

19. አቶ ጃለታ: (shouts from car) ስማ፣ ጥበቃ ጓድ! ምን ሆነሀል? ናና ቶሎ በሩን ክፈትልኝ! (to ንጉሴ) ንጉሴ፣ ልጄ፤ ተመልከት ይሀን ዘበኛ። የእኛ ዘበኛ ከሆነው ከዛ ሰካራም ሙሉቱ፣ የባሰ ነው። ማለቴ፣ ተመልከት ሴት ልጁ ከእርሱ ጋር እንድትጠብቅ ከቤት ይዟት መጥቶ እኮ ነው፤ ደግሞ ምን እንደሆነ አምላክ ይወቅ፤ ብቻ በወሬ ጠምዷታል እኮ!

20. ዘበኛ: ይቅርታ፣ ጌታዬ። ምን ልርዳዎት?

21. አቶ ጃለታ: (discussion in the background, under ምህረት thinking aloud) የትምህርት ቤቱን ርዕስ መምህር ማግኘት እንፈልጋለን።

22. ዘበኛ: ይችላል የመግቢያ ደብዳቤውን ማየት፤ ጌታው?

23. አቶ ጃለታ: (shouting out of the car window) ምን ይላል፤ የመግቢያ ደብዳቤማ አለን። ያለ መግቢያ ደብዳቤ የመጣን ይመስልሀል? ሰውዬ፣ በሩን ክፈት!

24. ምህረት: (thinking aloud while ዘበኛ and አቶ ጃለታ discuss) አሀ! እነዚህ ሀብታም ሰዎች ግን እንዲህ ቀለል ያለ ህይወት የሚኖራቸው ምን ሰርተው ይሆን? (wakes up) ኧንዴ ይህ የመጨረሻ እድሌ ነው! ልክ ጥበቃው በሩን ሲከፍት ጠብቄ ተንደርድሬ መግባት አለብኝ። በዚህ ሁኔታ ካልገባሁ ፈጽሞ አያስገባኝም!

25. ዘበኛ: እሺ፣ እባክዎን ይለፉ። በሩን እከፍትልዎታለሁ።

26. SFX: IRON GATE BEING OPENED BY HAND

27. SFX STEPS: ምህረት RUNS IN

28. ዘበኛ: (shouts) ሄይ! አንቺ! አንቺ ልጅ! ቁሚ! (to himself) አሀ እርጉም - አሁን በሩን ትቼ መሄድ አልችል! (shouting again) ያቺን ልጅ አስቁሙልኝ! ያዟት!

29. SFX: CAR DRIVES IN

30. SFX: IRON GATE CLOSING QUICKLY

31. MUSIC INTERLUDE

<u>SCENE 2: አቶ ሙሉቱ RECEIVES A CALL FROM HIS SISTER ወይዘሮ ለምለም, WHO LIVES ABROAD</u>

32. MORNING ATMO IN THE CITY, LIGHT TRAFFIC

33. SFX: MOBILE PHONE RINGING

34. ሙሉቱ: (answers call) ሃሎ?

35. ወይዘሮ ለምለም: (on the phone) ሃሎ፣ ሙላቱ፡፣ ወንድሜ፣ መናገር ትችላለህ? - መናገርማ በሚገባ ትችላለህ፣ ለካ ሁሌም መናገር ትችላለህ፡፡ (laughs out loud)

36. ሙላቱ: ለምለም፣ ስራዬን ልታከብሪልኝ ይገባል፡፡ ዘበኛ ነኝ፤

37. ወይዘሮ ለምለም: ትክክል! እዚያ ለሰዓታት ተጎልተህ ሰዎች ለስራ ሲወጡና ሲገቡ ታያለህ፡፡ እና ለመሆኑ አለቃህ በአካባቢው አለ?

38. ሙላቱ: የለም፡፡ ልጁን ወደ አዲሱ ትምህርት ቤቱ ይዞ እየሄደ ነው፡፡ የቤት ልጁ፣ የምህረት እኩያ የሆነ ወንድ ልጅ አለው፡፡ ለምለም ግን ምንድን እየሆነ ያለው? ቅዱስ እና ብሩክን ከወሰድሻቸው ጊዜ አንስቶ ጠፍተሻል፡፡

39. ወይዘሮ ለምለም: ኧረ ተረጋጋ፣ ወንድሜ፡፡ ሁሉ ነገር ሰላም ነው፡፡ ሁለቱ ቆንጆ ልጆችህ በጥሩ እንክብካቤ ያገኛሉ፡፡ ስማ፣ ጥቂት ገንዘብ ልኬልሀለሁ፡፡ እንደተለመደው መታወቂያህን ይዘህ ወደ ፖስታ ቤት ብትሄድ ገንዘብህን ታገኛለህ፡፡

40. ሙላቱ: ወይ፣ ለምለም፡፡ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በእውነቱ እህቴ ስለ ርዳታሽ፣ አመሰግንሻለሁ፡፡.

**KW BEGIN**

41. ወይዘሮ ለምለም: ምንም ችግር የለም፤ ለነገሩ እኮ ቤተሰቦች ነን። ስለ ቤተሰብ ካነሳን ዘንዳ፣ ሌሎቹስ እንዴት ናቸው? ሉሊትስ መቼ ነው የምተወልደው?

42. ሙላቱ: (with resignation) ቤተሰቤ ያው ነው፤ ምህረትም እያደገች እና ችግር እያመጣች ነው። ሉሊት፣ ባለቤቴ እንደሆነ ...መልካም ብቻ፣ ምን ማለት ይቻላል። ማርገዟን ቀጥላለች።

43. ወይዘሮ ለምለም: (chuckling) ኦህ ስማ፣ ሙላቱ:፤ ሉሊት ብቻዋን አታረግዝም። አርግዝናዉ የሁለት ሰው የጋራ ውጤት መሆኑን አትዘንጋ...

44. ሙላቱ: ልክ ነው። ብቻ ያም ሆነ ይሀ።

KW END

45. ወይዘሮ ለምለም: ወይጉድ, , , ስማ የኔ ወንድም......

46. ሙላቱ: ለምለም፣ ልጆቼን ላናግራቸው እችላለሁ?

47. ወይዘሮ ለምለም: (annoyed) ሙላቱ! ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ሲል ተነጋግረናል፣ አልተነጋገርንም? ቅዱስ እና ብሩክ ከሁኔታዎች ጋር ለመላመድ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፤ ታውቃለህ! አዲስ ሀገር፣ አዲስ ትምህርት ቤት፣ አዲስ ቋንቋ እና ሁሉም ነገር አዲስ ነው። ለጊዜው ባታናግራቸው መልካም ነው። ይልቁንስ ይበልጥ እንዲናፍቁ ያደርጋቸዋል።.

48. **ሙላቱ**: (politely) ልክ ነው፣ እሺ፣ ገብቶኛል፣ ግን …ለምለም…

49. **SFX: CALL SUDDENLY ENDED**

50. **ሙላቱ**: ሃሎ! ሃሎ! ለምለም … ለምለም፣ ይሰማሻል? ሃሎ? (sighs)

51. **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3: ምህረት AT PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ'S OFFICE**

52. **SFX: OFFICE AMBIENCE**

53. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ**: ምህረት፣ይሄ በጣም አስደንጋጭ ነው! ቆይ አሁን ስለ አባትሽ እቅድ የምትነግሪኝ ነገር በእርግጥ እውነት ነው? ይህ ትክክል ከሆነ ስለዚህ ጉዳዩ እርሳቸውን ማናገር ይኖርብኛል፡፡

54. **ምህረት**: እውነቴን ነው፣ ሁሉም ነገር እውነት ነው፤ ርዕሰ መምህርት፡፡ አባቴ ወደ ቦንጎ አካዳሚ መጥቼ ከሚያየኝ ይልቅ ለባል ቢሰጠኝ ይመርጣል! ማታ ይህንን ለእናቴ ሲነግራት ሰምቻለሁ፡፡ የተኛው ቢመስላቸውም እኔ ግን አልተኛሁም ነበር፡፡ (almost breaking down in tears) ቀኑ ከህይወቴ ሁሉ ምርጡ ቀን መሆን ይገባው የነበረ ቢሆንም አባቴ ግን ወደ መጥፎ ቀን ለወጠው፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ሳለቅስ ነዉ ያደርኩት፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡

55. ሰብለ: አይዞሽ፣ ምህረት! ስሚኝ! ላንቺ የተለየ ነገር አደርጋለሁ። ለመማር በጣም የጓጓሽ ትመስያለሽ እናስ ከአጠገብሽ ያለሁት ማን እመስልሻለሁ? ያንን እድል አልዘጋብሽም። የትምህርት ቤት መለያ «የደንብ ልብስ» ባይኖርሽም ትምህርት መጀመር ትችያለሽ። ቤተሰቦችሽ መግዛት እስኪችሉ ድረስ የቤት ልብስሽን ለብሰሽ ነይ። .

56. ምህረት: (trying to control her emotions) እትዬ ሰብለ! በእውነት- በእውነት በጣም አመሰግናለሁ...ምን ልል እችላለሁ? የቻልኩትን ሁሉ ለማድረግ ቃል እገባልለሁ! ባደረጉልኝ ነገርም አይጸጸቱም!

57. ሰብለ: እንደማልጸጸት ተስፋ አደርጋለሁ፤ ምህረት። እኔም ያልሽኝን ነገር ሁሉ አምኜ እቀበልሻለሁ። እንደነገርኩሽ ይህ ለየት ያለ ነገር ነው፤ እናም እርግጠኛ ነኝ በትምህርት ቤቱ የቦርድ ስብሰባ ላይ መነሳቱ እንደማይቀር፤ ያኔ ታዲያ ውሳኔዬን እንዲቀበሉት ለመከላከል ቆርጫለሁ። የሆኖ ሆኖ አባትሽን ማግኘት እና ማነጋገር እፈልጋለሁ። ነገ መጥተው እንዲያገኙኝ ንገሪያቸው።

58. ምህረት: እሺ፣ እነግረዋለሁ። በድጋሚ አመሰግናለሁ። ግን- እትዬ ሰብለ፣ ብቻ እንዴት ብዬ ልነግረዉ እንደምችል አላዉቅም? ልነግርዎ እንደመጣሁ ካወቀ በቁሜ ነዉ የሚዘለዝለኝ።

59. ሰብለ: አትጨነቂ፣ ቆይ ማስታወሻ ቢጤ ልፃፍልሽ፡፡

60. SFX: PEN SCRIBBLING ON PAPER

61. SFX: PAPER HANDED OVER

62. ሰብለ: ለአባትሽ ይህን ማስታወሻ ስጪያቸው፡፡ ያ በቂ ይመስለኛል፡፡

63. ምህረት: አሁንም በድጋሚ አመሰግናለሁ፣ እትዬ፡፡ ይህ ማለት ታድያ ትምህርት መጀመር እችላለሁ ማለት ነዉ?

64. ሰብለ: አዎ፣ ምህረት፡፡ ወደ ቦንጎ አካዳሚ እንኳን ደህና መጣሽ! አሁን ግን ሌሎች እንግዶች ማስተናገድ ስላለብኝ ላስወጣሽ ነው፡፡

65. SFX: STEPS - ምህረት LEAVING FAST

66. SFX: DOOR OPENS

KW BEGIN

67. SFX: TWO PEOPLE BUMP INTO EACH OTHER

68. ምህረት/ንጉሴ: (simultaneously) ኦህ - ይቅርታ!

69. አቶ ጃለታ: (angry) ሄይ፣ የምትረግጪውን እያየሽ!

70. ምህረት: ይቅርታ አላየሁህም፡፡

71. ንጉሴ: አባዬ፣ ጥፋቱ የእኔ ነዉ! የምረግጠውን ማየት የነበረብኝ እኔ ነኝ፡፡

72. **አቶ ጃለታ:** ምንም ይቅርታ መጠየቅ አያስፈልግም፣ ንጉሴ። (realizing who ምህረት is)እንዴ, , , -አንቺ? በሩ ላይ ያየንሽ ልጅ አይደለሽ? ለምንድን ነዉ መኪናዬን እየሮጥሽ የተከተልሽው? ደግሞስ እዚህ ምን ትሰሪያለሽ? ለመሆኑ እዚህ ለአንቺ የሚገባ ቦታ ነዉ?

73. **ንጉሴ:** አባዬ፣ ተው ባክህ! (to ምህረት) ይቅርታ...

74. **ሰብለ:** (Calls out) ተረኛ, , , ፣ ይግቡ!

**KW END**

75. **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 4: አቶ ሙላቱ AT HOME WITH HIS WIFE ወ/ሮ ሉሊት**

76. **EVENING ATMO IN THE SLUMS**

77. **SFX: DRINK BEING OPENED**

78. **ወ/ሮ ሉሊት:** እሺ። አሁን ለዚህ ሁሉ ነገር ገንዘቡን ከየት እንዳገኘኸ ትነግረኛ ? በወሩ አጋማሽ ላይ እንዲህ ጥምብዝ ብለህ ወደ እቤት መጣህ... ሙላቱ: እኔ እኮ ግራ ግብት ነው ያለኝ፤ ቆይ ባንክ ዘርፈህል እንዴ?

79. **ሙላቱ:** (indifferent, sips from bottle) እኔን እንደእዚያ ነው የምታስቢኝ ፣ ሉሊት?

80. ወ/ሮ ሉሊት፡ እስከ አሁን ድረስ ፖሊስ መጥቶ በራችንን አለማንኳኳቱም ገርሞኛል። ሙላቱ! ተናገር እንጂ ፤ ገንዘቡን ከየት ነዉ ያመጣኸዉ?

81. ሙላቱ፡ ግን ለምን ሁሌ ግራ ታስቢያለሽ?

82. ወ/ሮ ሉሊት፡ (bitter) ምክንያቱም ህይወታችን ግራ ስለሆነ ነዋ! ከጠዋት እስከ ማታ ሁሉ ነገራችን በመጥፎ ነገሮች የተሞላ ግራ! ቆይ! ለመሆኑ ቁርስ መብላት እንችላለን? ምሳስ? እራትስ? ሌላ ልጅ ልንወልድ ነው። ምን እናበላዋለን ፣ ምን ይጠጣል፣ ምን ይለብሳል? ወየጉድ እንዴት ዘነጋሁት፣ ጭራሽ የቤት ኪራዩም ገና አልተከፈለም!

83. ሙላቱ፡ (pretends to snore) ንዝንዛሽሽን ጨረስሽ? ለነገሩ በደንብ የሚዋጣልሽ ያ ነው። (angry) ለመሆኑ ምህረት የት ነች? እስከ አሁን እቤት መመለስ አልነበረባትም?

84. ወ/ሮ ሉሊት፡ ምህረት ከገባች ቆይታለች። አሁን ለምግብ ማብሰያ እና መታጠቢያ የሚሆን ውሃ ልትቀዳ ወጥታ ነው። ይህንን ወረቀት ያንብበው ብላ አስቀምጣልሀለች።.

85. ሙላቱ፤ (not pleased) ሌላ ደብዳቤ? ይህ ሁሉ ደብዳቤ እና ማስታወሻ ምንድን ነው? አሁን እኔ ደክሞኛል እባክሽ! በኋላ አነበዋለሁ።

86. ወ/ሮ ሉሊት፡ (still insisting) ሙላቱ፡፣ ገንዘቡን ከየት አመጣኸው? ለምህረት ባል አገኘህላት እንዴ? ለጥሎሽ የሚሆነዉን ገንዘብ ሰጡህ? ይሄ ሁሉ ገንዘብ ከእዝያ ነው አይደል? ለመሆኑ ሰዉየዉ ማን ነው?

87. ሙላቱ፡ (chuckles sheepishly) ሀሀሀሀሀሀ... ስለ ሴቶች የሚነገረዉ በሙሉ እውነት ነው፡፡ እውነትም የመጣችሁት ከሌላ ዓለም ነዉ!

88. SFX: IRON SHEET DOOR OPENING

89. ወ/ሮ ሉሊት፡ ምህረት፣ መጣሽ!

90. ምህረት፡ (panting from exhaustion) የውሃ ዋጋ ጨምሯል!

91. SFX: WATER CANS DROPPED ON THE FLOOR

92. ሙላቱ: (furious) የውሃ ዋጋ ጨመረ! የምግብ ዋጋ ጨመረ! ኪራይ ጨመረ! ሁሉም ነገር ጨመረ፣ ጨመረ፣ ጨመረ! ባለበት የቆመው የእኔ ደመወዝ ብቻ ነው!

93. ምህረት: (hesitating) አባዬ ልነግርህ የምፈልገው ነገር አለ...

94. MUSIC INTERLUDE

**95. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

በእዚሁ «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» በሚል ርዕስ በዶይቼ ቬለ የበማድመጥ መማር መርሃ-ግብር የተሰናዳዉ አዲስ ትምህርታዊ ድራማ ክፍል ሁለት ይጠናቀቃል። አቶ ሙላቱ የምህረት አስተማሪ የላኩትን ማስታወሻ ያነቡ ይሆን? ንጉሴ ዳንኤል እና ምህረትስ በቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመርያ የትምህርት ቀን ምን ያጋጥማቸዉ ይሆን? የእዚህን እና የሌሎችን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የሚቀጥለዉን ክፍል ድራማ ይከታተሉ። ስለዝግጅቶቻችን የበለጠ ለመረዳት dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገጽ አድራሻችን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን «like» ላይክን በመጫን የበማድመጥ መማር አድማጭ መሆንዎን ያሳዉቁን፤ ከድረ-ገጽ አድራሻችን ለግሎ ገልብጠው እንዲወስዷቸው የተዘጋጁ የድምፅ፣ የቪዲዮና ሌሎች ክምችቶችንም ያገኛሉ፤ በሚቀጥለዉ ዝግጅት እስክንገናኝ ጤና ይስጥልን።